ታህሳስ 26/2004 ዓ.ም.

# በጎፋ ልዩ ዞን በኡባ ወረዳ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት አባላት ጠቅላላ ጉባዔ አካሄዱ

*ለጽ/ቤቱ ማሠሪያ አንድ አባል ከራሳቸው ማሳ ላይ ቦታ ሰጥተዋል።*

በደቡብ ኢትዮጵያ በጎፋ ልዩ ዞን በኡባ ወረዳ የሚገኙ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) አባላት ታህሳስ 25/2004 ዓ.ም. የወረዳ ጠቅላላ ጉባዔ ማካሄዳቸውን አቶ እንድርያስ ኤሮ የመኢአድ ማዕከላዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባልና የደቡብ ቀጠና ኃላፊ ለመኢአድ ህዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ አስታወቁ።

በጠቅላላ ጉባዔው ላይ የተሳተፉት የኡባ ወረዳ የመኢአድ አመራር አባላት ቁጥራቸው 50 እንደሆነና በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ፣ የገዥው ፓርቲ ባካባቢያቸው እያደረሰባቸው ስላላለው ጫና እንዲሁም ስለመኢአድ ውይይት ያካሄዱ መሆናቸውን አቶ እንድርያስ ኤሮ ገልጸዋል።

የመኢአድ ኡባ ወረዳ ጽ/ቤት አገልግሎት የሚሰጠው በጊዜያዊነት በመሆኑ በቋሚነት የሚያገለግል ጽ/ቤት ለመሥራት ጉባዔተኞቹ መስማማታቸውንና ለቤቱ መሥሪያ የሚያገለግል ቦታም አንዱ አባል ከራሳቸው ማሳ ላይ እንደሚሰጡ ቃል መግባታቸውን የደቡብ ቀጠና ኃላፊው ጨምረው አስረድተዋል። ለቢሮው መሥሪያም በዕለቱ ከተገኙት ተሰብሳቢዎች ብር 1,450.00 መዋጣቱን አቶ እንደርያስ ጠቁመው መዋጮውን ሌሎች አባላት የሚቀጥሉ መሆናቸውንም ተናግረዋል።